ታህሳስ 2 ቀን 2012 ዓ.ም

# ማስታወቂያ

## ትምህርት በአግባቡ እየተካሄደባቸው ባልሆኑ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግቢዎች ለሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ

በአገሪቱ በተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተፈጠሩ አለመረጋጋቶችን እንዲሁም ተያያዥ ምክንያቶችን በማንሳትና ስጋት እንዳለባቸው በመጥቀስ የአንዳንድ የባሕር ዳር ዩኒቨርሰቲ ግቢዎች ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ እየተከታተሉ እንዳልሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የዩኒቨርሲቲው አመራር፤ የተቋሙ የተለያዩ አካላትና የተማሪዎች አመራሮች ከከተማው አስተዳደር፣ የጸጥታ አካላትና የከተማው ወጣቶች ጋር በቅንጅት ሲያደርጓቸው በቆዩአቸው ስራዎች በዩኒቨርሰቲው አንዳንድ ግቢዎች ሰላማዊ መማር ማስተማር ቀጥሏል፡፡

ይህንን ሁኔታ በማጤን የባሕር ዳር ዩኒቨርሰቲ ሴኔት ታህሳስ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ በጉዳዩ ላይ በስፋት በመወያየትና እያንዳንዱ ግቢ ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ በመገምገም የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል፡-

1ኛ. ትምህርት በተቋረጠባቸው ግቢዎች ከታህሳስ 2 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት በመደበኛ ሁኔታ እንዲቀጥል፤

2ኛ. ትምህርት እየተከታተሉ ያልሆኑ ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዲገኙ፤ ነገር ግን እነዚህ ተማሪዎች እስከ ሰኞ ታህሳስ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ በትምህርት ገበታቸው ላይ የማይገኙ ከሆነ ከዩኒቨርሲቲው በራሳቸው ፈቃድ እንደተሰናበቱ እንዲያውቁት፤

3ኛ. ትምህርት ከተጀመረም በኋላ ደጋግሞ ማቋረጥን እንደስልት በመውሰድ ችግሮች እንዲቀጥሉ የማድረግ እንቅስቃሴዎች በአንዳንድ ግቢዎች ሲታዩ እንደነበር ሴኔቱ ገምግሞ ይህ ጉዳይ ደግሞ ቢከሰት ደግመው ያቋረጡ ተማሪዎች በራሳቸው ፈቃድ ከዩኒቨርሰቲው የመሰናበት ውሳኔ በራሳቸው ላይ እንደወሰኑ ቆጥሮ ይህን ተፈጻሚ ለማድረግ ወስኗል፡፡

*የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሴኔት*